# ከባህር ዳር ተይዞ ማዕከላዊ ጨለማ ቤት ታስሮና ይፈታል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው አቶ ገበየሁ ፋንታሁን ህይወቱ አለፈ

**(ጌታቸው ሽፈራው)**

በእነ እስከዳር ይርጋ ክስ መዝገብ በ"በሽብር" ክስ አራት አመት ተፈርዶበት ይፈታል ተብሎ እየተጠበቀ የነበረው 2ኛ ተከሳሽ ገበየሁ ፈንታሁን በእስር ቤት ባጋጠመው የጤና እክል ህይወቱ አልፏል። ተከሳሹ በቂ ሕክምና ባለማግኘቱ ከደከመ በኋላ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ተወስዶ ትናንት የካቲት 18/2010 በፖሊስ ሆስፒታል ህይወቱ አልፏል።

ገበየሁ ፈንታሁን ማዕከላዊ 8 ቁጥር በሚባል ጨለማ ቤት ታስሮ እንደነበርና በቆይታው ድብደባ እንደደረሰበት በወቅቱ አብሮ ታስሮ የነበረው ጓደኛው ገልፆአል። በተለይ በአንድ ወቅት ከደረጃ ገፍትረው እንደጣሉትና በዚህም ምክንያት የራስ ህመም እንደነበረበት ተገልፆአል። አቶ ገበየሁ ፋንታሁን በታመመበት ወቅት በቂ ህክምና እንዳላገኘ ጓደኛው ገልፆአል።

አቶ ገበየሁ ፋንታሁን የአንድ ልጅ አባት እና ባለትደር እንደነበርና ከባህርዳር ተይዞ እስከታሰረበት ጊዜ ድረስ በሾፌርነት ተቀጥሮ ቤተሰቦቹን ያስተደድር እንደነበር ተገልፆአል። በክስ መዝገብ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ገበየሁ ፋንታሁን አራት አመት ተፈርዶበት የነበር ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ እስከዳር ይርጋ ጥር 9/2010 ዓም ተፈትቷል። አቶ ገበየሁ ፋንታሁን ይፈታል ተብሎ እየተጠበቀ እንደነበር ታውቋል።



ቤተሰቦቹ መፈታቱን ሲጠባበቁ በእስር ላይ የሞተው የባህርዳር ቀበሌ 14 ወንድማችን ገበየሁ ፋንታሁን ይህ ነበር!! እንደርሱ የተከሰሰው ጓደኛው ከተፋታ ሳምንት አልሞላውም። ገበየውም ነገ ዛሬ መጣ ሲባል አስከሬን ውሰዱ ተባሉ።